# ትምህርት 16

1. የቃየንና የዘሮቹ የሕይወታቸው ዓላማ ምን ነበር?

ሀ- የቃየንና የዘሮቹ የሕይወታቸው ዓላማ ርካታ ማግኘትና ገንዘብና ንብረት መሰብሰብ ብቻ ነበር።

2. ቃየን አቤልን ስለ ገደለው ሰይጣን እግዚአብሔር ሊያደርገው የወሰነውን ነገር ማስቀም ችሎ ነበር?

ሀ- አልቻለም።

ለ- እግዚአብሔር ሊያደርገው የወሰነውን ነገር ማንም ሊያስቀመው አይችልም።

3. ቃየን አቤልን ስለ ገደለ እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ የገባውን ቃል ረሳ?

ሀ- አልረሳም።

ለ- እግዚአብሔር የገባውን ቃል አይረሳም።

4. እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ሴት የተባለ ሌላ ልጅ የሰጣቸው ለምንድን ነው?

ሀ- ቃየን አቤልን ስለ ገደለው እግዚአብሔር ከሴት ዘር አዳኝን ለመላክ ስለ ወሰነ ነው።

5. አዳምና ሔዋን ለምን ሞቱ?

ሀ- አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እምቢ ስላልሉና ሰይጣንን ስለታዘዙ።

6. ሰዎች ሁሉ የሚሞቱት ለምንድን ነው?

ሀ- በኃጢአታችን ምክንያት።

7. እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣው በምንድን ነው?

ሀ- በሞት

8. ሄኖክ ስለ ራሱ ምን ያውቅ ነበር?
ሀ- ሄኖክ የአዳምና የሔዋን ልጅ ሆኖ መወለዱን ያውቅ ነበር።
ለ- ሄኖክ ከዔድን የአትክልት ስፍራ ውጭ መወለዱን ያውቅ ነበር።
ሐ- ሄኖክ ኃጢአት ባለበት ዓለም መወለዱን ያውቅ ነበር።
መ- ሄኖክ ሞት ባለበት ዓለም መወለዱን ያውቅ ነበር።

9. ሄኖክ ስለ እግዚአብሔር ምን ያውቅ ነበር?
ሀ- ሄኖክ እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ያውቅ ነበር።
ለ- ሄኖክ እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት በሞት እንደሚቀጣ ያውቅ ነበር።
ሐ- ሄኖክ እግዚአብሔር ብቻ ከኃጢአቱ ሊያድነው እንደሚችል ያውቅ ነበር፡
መ-ሄኖክ እግዚአብሔር ሰዎችን ከሰይጣን ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ ያምን ነበር።

10. በሄኖክ ላይ የደረሰው እንግዳ ነገር ምንድን ነው?
ሀ- እግዚአብሔር ሄኖክ ከእርሱ ጋር እንዲኖር ወደ መንግሥተ ሰማይ መውሰዱ ነው።

11. መንግሥተ ሰማይ ምን ይመስላል?
ለ- መንግሥተ ሰማይ ኀዘን ወይም ልቅሶ ወይም በሽታ ወይም ሞት የሌለበት እጅግ ውብ ነው።

12. እግዚአብሔር ሄኖክን ወደ መንግሥተ ሰማይ ለምን ወሰደው?
ሀ- ሄኖክ እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘ ነው።
ለ- ሄኖክ ወደ እግዚአብሔር የቀረበው በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ሄኖክን ወደ መንግሥተ ሰማይ ከወሰደው በኋላ ብዙ ዓመታት አለፉ እጅግ ብዙ ሰዎችም በምድር ላይ ተወለዱ።

- የሴትና የሄኖክ ዘር እግዚአብሔርን በመከተል ሲቀጥሉ ሌሎች ብዙ ሕዝቦች ግን ሰይጣንን ይታዘዙ ነበር።

ዘፍጥረት 6፡1-2

1- ሰዎች በምድር ላይ እየበዙ ሲሄዱ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው።

2- የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች የሰዎችን ሴቶች ልጆች ውብ ሆነው አዩአቸው፤ ከመካከላቸውም የመረጧቸውን አገቡ።

- የእግዚአብሔር ልጆች እነማን ነበሩ?
- የሴት ዘር የሆኑ ሰዎች ነበሩ።

- እነርሱም በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ነበሩ።

- የሰዎች ሴቶች ልጆች እነማን ነበሩ?
- የቃየን ዘር የሆኑት ሴቶች ነበሩ።

- እነርሱም በእግዚአብሔር የማያምኑ ሴቶች ነበሩ።

- የሴት ዘር የሆኑት ወንዶች የቃየን ዘር የሆኑትን ሴቶች ምን አደረጉ?

- የሴት ዘር የሆኑት ወንዶች የቃየን ዘር የሆኑትን ሴቶች ማግባት ጀመሩ።

- በእግዚአብሔር ያመኑት ወንዶች በእግዚአብሔር ያላመኑትን ሴቶች ማግባት ጀመሩ።

- የሴት ዘር የሆኑት ወንዶች የቃየን ዘር የሆኑትን ሴቶች ማግባት በጀመሩ ጊዜ ምን ሆነ?

- እጅግ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መስማት የማይፈልጉ ሆኑ።

- እጅግ ብዙ ሰዎች የሰይጣንን ትዕዛዝ ብቻ መስማት የሚፈልጉ ሆኑ።

- እጅግ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድ የማይፈልጉ ሆኑ።

- እጅግ ብዙ ሰዎች የራሳቸውን መንገድ ብቻ የሚከተሉ ሆኑ።

- እጅግ ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን ያለመታዘዛቸው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ይመስላችኋል?

ዘፍጥረት 6፡3

3- እግዚአብሔርም «ሰው ሟች ስለሆነ መንፈሴ እያዘነ ከእርሱ ጋር ለዘላለም አይኖርም፤ ዕድሜው 120 ዓመት ይሆናል» አለ።

- እግዚአብሔር አብዛኛው ሰው እርሱን ባለመፈለጉ ደስ አላለውም።

- እግዚአብሔር ሰዎች እንዲታዘዙት የፈለገው ለምን ነበር?

- ሰዎች እንዳይጠፉ ስለ ፈለገ ነው።

- እግዚአብሔርም «ለሰዎች የምናገረው 120 ዓመት ብቻ ነው» አለ።

- ሰዎች አሁንም የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ባለመፈለግ ከጸኑ እግዚአብሔር ምን ደርጋል?

- እግዚአብሔር በሞት ይቀጣቸዋል።

- እግዚአብሔር ለሰዎች ይናገር የነበረው እንዴት ነው?

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ልብ ይናገር ነበር።

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ምን ይነግራቸው ነበር?

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ፥ ለሰይጣንን ግን እንዳይታዘዙ ይነግራቸው ነበር።

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ፥ የራሳቸውን መንገድ ግን እንዳይከተሉ ይነግራቸው ነበር።

- ሰይጣንስ ለሰዎች ልብ ይናገራል?
- አዎን።

- ሰይጣን ለሰዎች የሚነግራቸው ምንድን ነው?

- ሰይጣን ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይታዘዙት ይነግራቸዋል።

- ሰይጣን ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይታዘዙት የሚፈልገው ለምንድን ነው?

- ሰይጣን ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይታዘዙት የሚፈልገው ሰዎች እንዲጠፉ ስለሚፈልግ ነው።

- እግዚአብሔር ለልባችሁ የሚናገረውን ልትሰሙት ካልፈለጋችሁ እግዚአብሔር ይቀጣችኋል።

- እግዚአብሔርን መስማት ሰይጣንን ከመስማት የተሻለ አይደለምን?

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሲናገራቸው ሰዎች ለእግዚአብሔር ታዘዙ?

ዘፍጥረት 6፡11

11- ምድር በእግዚአብሔር ፊት በክፉ ሥራ ረከሰች፤ በዐመፅም ተሞላች። »

- ምንም እንኳን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ቢናገርም ብዙ ሰዎች ለእግዚአብሔር መታዘዝ አልፈለጉም።

- ምድርም በሰዎች ዐመፅ ተሞላች።

- በኖኅ ዘመን የነበሩት ሰዎች ምን አይነት ሰዎች ነበሩ?

- ራስ ወዳዶች ነበሩ።
- ስግብግቦች ነበሩ።

- በሌሎች ሰዎች ይቀኑ ነበር።
- ሌሎችን ሰዎች ያታልሉ ነበር።

- ለሌሎች ውሸት ይናገሩ ነበር።

- የሌሎችን ክፋት ያወሩ ነበሩ።
- ሌሎችን ሰዎች ይጠሉ ነበሩ።

- ክፉዎች ነበሩ።

- ዐመፀኞች ነበሩ።

- እርስ በርስ ይዋጉ ነበር።

- ብዙ ሰዎችን ይገድሉ ነበር።

- የእግዚአብሔርን መንገድ የማይፈልጉ ነበሩ።

- የራሳቸውን መንገድ ብቻ ይፈልጉ ነበር።

- የአሁኑ ዘመን ሰዎች በኖኅ ዘመን የነበሩትን ይመስላሉ?
- አዎን።

- የአሁኑ ዘመን ሰዎች ራስ ወዳዶችና ስግብግቦች ናቸው?
- አዎን።

- የአሁኑ ዘመን ሰዎች የሚዋሹና ስለሌሎች ክፉት የሚያወሩ ናቸው?
- አዎን።

- የአሁኑ ዘመን ሰዎች ከሌሎች ጋር የሚዋጉና የሚገዳደሉ ናቸው?
- አዎን።

- የአሁኑ ዘመን ሰዎች የራሳቸውን እንጂ የእግዚአብሔርን መንገድ የማይፈልጉ ሰዎች ናቸው?

- አዎን።

- እነዚያ ሰዎች ኃጢአተኛ ሆነው የተወለዱት የአዳምና የሔዋን ዘር ስለሆኑ ነው።

- የአሁኑ ዘመን ሰዎችም ኃጢአተኛ ሆነው የተወለዱት እነርሱም የአዳምና የሔዋን ዘር ስለሆኑ ነው።

- ሁላችንም የአዳምና የሔዋን ዘር ስለሆንን፥ ሁሉም ሰው ኃጢአተኛ ሆኖ ተወልዷል

- እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት አይቷል?

ዘፍጥረት 6፡5 & 12

5- እግዚአብሔር አምላክ የሰው ዐመፅ በምድር ላይ የበዛና የልቡም አሳብ ዘወትር ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመለከተ።

12- እግዚአብሔር ምድር ምን ያህል በክፉ ሥራ እንደ ረከሰች አየ፤ እነሆ፤ ሰው ሁሉ አካሄዱን አበላሽቶ ነበርና።

- እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት አይቷል?

- አዎን እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን በሙሉ አይቷል።

- እግዚአብሔር እያንዳንዱን ኃጢአት ያያል።

- እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ ስለ አለ ማንም ሰው ምንም ዓይነት ኃጢአት ከእግዚአብሔር መደበቅ አይችልም።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት ያያል ሁሉንም ኃጢአት ይቀጣል።
- እግዚአብሔር ሁሉንም ኃጢአት ያያል ሁሉንም ኃጢአት በሞት ይቀጣል።

- እግዚአብሔር የሰዎችን ሁሉ ኃጢአት አይቶ ምን አሰበ?

ዘፍጥረት 6፡6-7

6- እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ። ልቡም እጅግ አዘነ።

7- ስለዚህም እግዚአብሔር፣ «የፈጠርሁትን የሰው ዘር ከምድረ ገጽ አጠፋለሁ፤ ከሰው እስከ እንስሳ በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጡራን እስከ ሰማይ ወፎች... ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና» አለ።

- እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ስለ ሠሩ በጣም አዘነ።

- ምድር በሰዎች ኃጢአት ስለ ተሞላች እግዚአብሔር ምን ሊያደርግ ወሰነ?

- እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ለማጥፋት ወሰነ።

- ምድር በሰዎች ኃጢአት ስለ ተሞላች እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚኖሩትን ሕይወት ያላቸውን ፍጥረቶች ሁሉ ለማጥፋት ወሰነ።

- እግዚአብሔር በንግግር ብቻ ያቆመ ይመስላችኋል?

- ወይስ እግዚአብሔር ሊያደርግ ያሰበውን ሁሉ አድርጓል?

- እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እርሱ ከከለከላቸው ፍሬ ከበሉ እንደሚሞቱና ከእርሱ እንደሚለዩ ነግሯቸው ነበር።

- ታዲያ እግዚአብሔር የተናገረውን አደረገ ወይስ በንግግር ብቻ ተወው?

- እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ያለውን አድርጓል።

- እግዚአብሔር ቃየንንና አቤል በእርሱ መንገድ ብቻ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደሚችሉ አለበለዚያ ተቀባይነት እንደማያገኙ ነገራቸው።

- ታዲያ እግዚአብሔር የተናገረውን አደረገ ወይስ በንግግር ብቻ ተወው?

- እግዚአብሔር አደርገዋለሁ ያለውን አድርጓል።

- እግዚአብሔር እንደ ሰዎች አይደለም።

- ሰዎች አንድን ነገር አደርጋለሁ ይላሉ ሆኖም አያደርጉትም።

- እግዚአብሔር ግን እንደ ሰዎች አይደለም።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ አደርጋለሁ ያለውን ያደርጋል።

- ከእግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት የተነሣ እግዚአብሔር ሊያጠፋው ያልፈለገው አንድ ሰው ነበረ።

ዘፍጥረት 6፡8-10

8- ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን አገኘ።
9- የኖኅ ታሪክ እንደሚከተለው ነው። ኖኅ በዘመኑ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ጻድቅና ከበደል የራቀ ሰው ነበር፤ አካሄዱንም ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።
10- ኖኅም ሴም፣ ካምና ያፌት የሚባሉ ሦስት ወንዶች ልጆች ነበሩት።

- እግዚአብሔር ኖኅን ላለማጥፋት የወሰነው ለምን ነበር?

- ኖኅ ምንም ዓይነት ኃጢአት ስላልሠራ ነው?
- አይደለም።

- ኖኅ የተወለደው እንደ ማንኛውም ሰው ኃጢአተኛ ሆኖ ነው።
- ኖኅ የተወለደው እንደ ማንኛውም ሰው የሰይጣን ባሪያ ሆኖ ነው።

- ታዲያ እግዚአብሔር ኖኅን ላለማጥፋት የወሰነው ለምን ነበር?

- ኖኅ የሰይጣን ትዕዛዝ ስላልሰማ ነው።

- ኖኅ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለሰማ ነው።

- ኖኅ የራሱን መንገድ ስላልተከተለ ነው።

- ኖኅ የእግዚአብሔርን መንገድ ብቻ ስለ ተከተለ ነው።

- ኖኅ አዳኝን ይጠባበቅ ስለ ነበረ ነው።

- እግዚአብሔር ኖኅን ለማዳን የወሰነው ለምን ነበር?

- ኖኅ ኃጢአተኛ ሆኖ መወለዱን ያውቅ ስለ ነበረ ነው።

- ኖኅ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ያውቅ ስለነበረ ነው።

- ኖኅ እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ ያውቅ ስለ ነበረ ነው።

- ኖኅ ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያውቅ ስለ ነበረ ነው።

- ኖኅ እግዚአብሔር ከኃጢአቱ የሚያድነውን አዳኝ እንደሚልክለት ያውቅ ስለ ነበረ ነው።

- ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ እግዚአብሔር ኖኅን ላለማጥፋት ወሰነ።
- ጸጋ ምንድን ነው?

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡-

- አንድ ሌባ የጐረቤቱን ንብረት ሁልጊዜ ይሰርቅ ነበር።

- አንድ ቀን ሌባውን ጐርፍ ወሰደው።

- ሌባው በወንዙ ውስጥ ሊሰምጥ ጥቂት ቀርቶት ነበር።

- ነገር ግን ያ ጐረቤቱ ሌባውን አይቶ፥ ከወንዙም ውስጥ ጐትቶ በማውጣት አዳነው።

- ሌባው ብዙ ጊዜ ቢሰርቀውም ጐረቤቱ ግን አዳነው።

- ሌባው መስመጥ ቢገባውም ጐረቤቱ ግን አዳነው።

- ይህ ጸጋ ነው።
- እግዚአብሔር ስላመንነው ብቻ የሚያድነን በዚሁ ዓይነት ነው።

- ኖኅ በእግዚአብሔር ስላመነ እግዚአብሔርም ኖኅን ሊያድነው ስለ ወሰነ እግዚአብሔር ኖኅን አዘዘው።

ዘፍጥረት 6፡13-14

13- ስለዚህ እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው፡- «ሰውን ሁሉ ላጠፋ ነው፤ ምድር በሰው ዐመፅ ስለ ተሞላች በእርግጥ ሰውንም ምድርንም አጠፋለሁ።
14- አንተ ግን በጎፈር እንጨት መርከብ ሥራ፤ ለመርከቧም ክፍሎች አብጅላት፤ ውስጧንና ውጭዋን በቅጥራን ለብጠው።»

- እግዚአብሔር ኖኅ ምን እንዲያደርግ አዘዘው?

- እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ አዘዘው።

- እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ያዘዘው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ሕይወት ያለውን ፍጥረት ሁሉ ከምድር ላይ ለማጥፋት ጐርፍን ስለሚሰድድ ነው።

- እግዚአብሔር ኖኅ መርከብን እንዴት መሥራት እንዳለበት ብዙ ትእዛዛትን ሰጥቶታል።

ዘፍጥረት 6፡15-21

15- እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው «እንዲህ አድርገህ ሥራት፡- ርዝመቷ 140 ሜትር፣ ወርዷ 23 ሜትር፣ ከፍታዋ 13.5 ሜትር፣ ይሁን።

16- ለመርከቧ ጣራ አብጅላት፣ ጣራና ግድግዳዋ በሚጋጠምበት ቦታ ግማሽ ሜትር ክፍተት ተው፤ ከጐኗ በር አውጣላት፤ ባለ ሦስት ፎቅ አድርገህ ሥራት።

17- እኔም ከሰማይ በታች የሕይወት እስትንፋስ ያለባቸውን ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ለማጥፋት እነሆ በምድር ላይ የጥፋት ውሃ አወርዳለሁ፤ በምድር ላይ ያለ ሁሉ ይጠፋል።

18- ካንተ ጋር ግን ቃል ኪዳን እመሠርታለሁ። አንተና ወንዶች ልጆችህ፣ ሚስትህና የልጆችህ ሚስቶች ከአንተ ጋር ወደ መርከቧ ትገባላችሁ።

19- ከአንተ ጋር በሕይወት እንዲቈዩ ከሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ተባዕትና እንስት እያደረግህ ሁለት ሁለቱን ወደ መርከቧ ታስገባለህ።

20- ከእያንዳንዱ የወፍ ወገን፣ ከእያንዳንዱ የእንስሳ ወገን፣ በምድር ላይ ከሚሳቡ ፍጥረት ሁሉ በየወገናቸው በሕይወት ይቈዩ ዘንድ ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደ አንተ ይመጣሉ።

21- ለአንተና ለእነርሱ የሚያስፈልገውን ምግብ ሁሉ አከማች። »

- እግዚአብሔር ኖኅን በተሰጠው ርዝመት አንድ መርከብ እንዲሠራ አዘዘው።

- እግዚአብሔር ኖኅ በተሰጠው ስፋት መርከብ እንዲሠራ አዘዘው።

- እግዚአብሔር ኖኅ በተሰጠው ከፍታ መርከብ እንዲሠራ አዘዘው።

- እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ ያዘዘው ኖኅ በሚፈልገው ዓይነት ነበር?

- አይደለም።

- እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ የፈለገው ኖኅ በሚፈልገው ዓይነት አይደለም።

- እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ የፈለገው እንዴት ነበር?

- ልክ እግዚአብሔር በዘዘው ዓይነት ነው።

- እግዚአብሔር ኖኅ መርከቡን እንዲሠራ የፈለገው ልክ እግዚአብሔር እርሱን ባዘዘው መሠረት ነው።

- እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ እንዲሠራ የፈለገው በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ነው።

- የአዳምና የሔዋን ልብሶች መሠራት የነበረባቸው እግዚአብሔር በሚፈልግበት መንገድ ብቻ ነበር።

- የቃየንና የአቤል መሥዋዕቶች መቅረብ የነበረባቸው፥ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ብቻ ነበር።

- የኖኅም መርከብ መሠራት የነበረበት እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ብቻ ነበር።

- እግዚአብሔር ኖኅ እንዲሠራ ያዘዘው ስንት መርከብ ነበር?

- አንድ መርከብ ብቻ።

- ኖኅ የሚድንበት አንድ መርከብ ብቻ ነበር።

- ኖኅ የሚድንበት ሌላ መርከብ አልነበረም።

- እግዚአብሔር ኖኅ ለመርከቡ ስንት በር እንዲያደርግ አዘዘው?

- አንድ በር ብቻ።

- ኖኅ ወደ መርከቡ ገብቶ የሚድንበት አንድ በር ብቻ ነበር።

- ኖኅ ወደ መርከቡ ገብቶ የሚድንበት ሌላ በር አልነበረም።

- ኖኅ እግዚአብሔርን ታዝዞ?

ዘፍጥረት 6፥22

22- ኖኅም ሁሉን እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ።

- ኖኅ በእግዚአብሔር አመነ።
- ኖኅ እግዚአብሔር እንደማይዋሽ አመነ።

- ኖኅ እግዚአብሔር እንደ ተናገረው የጥፋት ውኃ እንደሚልክ አመነ።

- ስለዚህ ኖኅ ልክ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት መርከብ ሠራ።

- ከዚያ በፊት ዝናብ አይቶ የማያውቀው ኖኅ ያመነው ምንን ነበር?

- እግዚአብሔር የጥፋት ውሃ እንደሚሰድድ።

- ከዚያ በፊት ሰዎች ሁሉ ዝናብ ሲዘንብ አይተው ባያውቁም፤ ኖኅ ያመነው ምንን ነበር?

- እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ እንደሚልክ።

- ኖኅ መርከቡን እየሠራ ምን ያደርግ ነበር?

- ኖኅ መርከቡን እየሠራ፥ ሰዎች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዲሰሙ ይነግራቸው ነበር።

- ኖኅ መርከቡን እየሠራ፥ ሰዎች በእግዚአብሔር እንዲያምኑ ይነግራቸው ነበር።

- ኖኅ መርከቡን በመሥራት ላይ እየሠራ እግዚአብሔር ምድርን ሁሉ ለማጥፋት የጥፋትን ውኃ እንደሚልክ ለሰዎች ነገራቸው።

- እኔ ለእናንተ ስለ እግዚአብሔር እንደምነግራችሁ ሁሉ ኖኅም ለሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር ነገራቸው።

- ሰዎች ኖኅን የሰሙት ይመስላችኋል?

- ይህንን በሚቀጥለው ትምህርት እንመለከታለን።